**USDA ጸረ መድልዎ መግለጫ**

በፌደራል የሲቪል መብቶች ህግ እና በU.S. የግብርና መምሪያ (USDA) የሲቪል መብቶች መተዳደሪያ ደንቦች እና ፖሊሲዎች መሰረት USDA፣ ኤጀንሲዎቹ፣ ጽህፈት ቤቶች እና ሰራተኞች እንዲሁም በ USDA ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ወይም የሚሰጡ ተቋማት በዘር፣ ቀለም፣ ብሔራዊ አመጣጥ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ የአካል ጉዳት፣ እድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ/የወላጅነት ሁኔታ፣ ከህዝብ የእርዳታ ፕሮግራም በሚገኝ ገቢ፣ በፖለቲካ እምነቶች ወይም ቀደም ሲል ለተደረገ የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ በቀል ወይም ብቀላ ላይ ተመስርቶ በማንኛውም በ USDA በሚካሄድ ወይም የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግለት ፕሮግራም ወይም ተግባር ውስጥ **መድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው** (ሁሉም መሰረቶች ለሁሉም ፕሮግራሞች ተፈጻሚ አይሆኑም)። የመፍትሄዎች እና ቅሬታ ማቅረቢያ ቀነ ገደቦች እንደ ፕሮግራሙ እና እንደክስተቱ ይለያያሉ።

የፕሮግራም መረጃ ለማግኘት አማራጭ የግንኙነት ዘዴዎች የሚያስፈልጓቸው አካል ጉዳተኛ ሰዎች (ለምሳሌ ብሬይል፣ በትልልቅ ፊደላት የታተመ፣ የድምጽ መቅጃ ቴፕ፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ፣ ወዘተ) ፕሮግራሙን የሚያስተዳድር የግዛት ወይም የአካባቢ ኤጀንሲን ሊያነጋግሩ ወይም በ711 ላይ በመገናኛ የመልዕክ ማሰራጫ አገልግሎት (Telecommunications Relay Service) አማካኝነት USDAን ሊያነጋግሩ ይገባል(ድምጽ እና TTY)። በተጨማሪ፣ የፕሮግራም መረጃ ከእንግሊዘኛ ውጪ ባሉ ቋንቋዎች እንዲኖር ይደረጋል።

የፕሮግራም መድሎ ቅሬታ ለማቅረብ፣ የ USDA ፕሮግራም የመድልዎ ቅሬታ ቅጽ AD-3027ን ይሙሉ፣ ይህም በመስመር ላይ የፕሮግራም መድልዎ ቅሬታ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል በሚለው ላይ እና በማንኛውም የ USDA ጽህፈት ቤት ይገኛል ወይም ለ USDA ደብዳቤ ይጻፉ እና በቅጹ ላይ የተጠየቀውን መረጃ ሁሉ በደብዳቤው ላይ ያቅርቡ። የቅሬታ ቅጽ ቅጂ ለመጠየቅ፣ ወደ (866) 632-9992 ይደውሉ። የተሞላውን ቅጽዎን ወይም ለ USDA የተጻፈውን ደብዳቤ ያቅርቡ በ፣

(1) ደብዳቤ፡- የU.S. የግብርና መምሪያ፣ የሲቪል መብቶች ረዳት ጸሃፊ ቢሮ፣1400 Independence Avenue, SW, Mail Stop 9410, Washington, D.C. 20250-9410፤

(2) ፋክስ፡ (202) 690-7442፤ ወይም

(3) ኢሜይል፡- program.intake@usda.gov

USDA እኩል እድል አቅራቢ፣ አሰሪ እና አበዳሪ ነው።